ነገረ ቅዱሳን

ለአብነት ትምህርት ተማሪዎች ሥልጠና ለመስጠት የተዘጋጀ የማስተማሪያ ጽሑፍ

በቅዱሳት መካናት ልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት አብነት ት/ቤቶች ተዘጋጀ

□□ጅ ዓ.ም

ማውጫ

1. መግቢያ.....2
2. . ትርጉም.....3
3. . የቅዱሳን ሕይወት.....3
4. . የቅዱሳን አሰያየም.....5
5. . የቅዱሳን ማንነት.....6
6. . የቅዱሳን አስተዋጽኦ.....11
7. . ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን /ቅዱሳት/.....13
8. ማጠቃለያ.....17
9. ዋቢ ማጣቀሻ መጻሕፍት.....18

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

1. መግቢያ

ነገረ ቅዱሳን በሚለው በዚህ ርእስ ስር ለመነሻ የሚሆኑ ጥቂት ቁም ነገሮች ብቻ ተካትተው ቀርበዋል። ትምህርቱ በጣም ሰፊ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ ለሚማሩ ሰዎች መጠነኛ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ ይችላል በማለት ባጭሩ ሊዘጋጅ ችሏል።

ይህ ጽሑፍ በሁለት የተለያዩ አካላት እጅ ሊገባ ይችላል። እነዚህም፥-

1 ኛ. መምህራነ ወንጌል ወይም አሠልጣኞችና

2 ኛ. ምእመናን ወይም ሠልጣኞች ናቸው። አሠልጣኞች ይህን የመነሻ ጽሑፍ መሠረት በማድረግ ሌሎች በዋቢነት የተጠቀሱና ያልተጠቀሱ ተጨማሪ መጻሕፍትን በማንበብ ከርእሰ ጉዳዩ ሳይወጡ አጣጥመውና አዳብረው በማቅረብ ረገድ ብዙ ይጠበቅባቸዋል። ሠልጣኞች ደግሞ ይህን ጽሑፍ ደጋግሞ በማንበብ ለመረዳትና ግልጽ ያልሆነውን በመጠየቅ በሚገባ ለማወቅና ባወቁትና በተረዱት መሠረት ለመኖር መታገል አለባቸው። ደረጃ በደረጃ እያደጉ በዋቢነት የተጠቀሱትን መጻሕፍት በማንበብ የበለጠ ለመረዳት ጥረት ሊያደርጉም ይገባቸዋል እንላለን።

ይህ ጽሑፍ ታላቁን ዐቢይ ርእሰ #ነገረ ቅዱሳን$ በማለት ሲያቀርብ በስሩ 6 /ስድስት/ ንዑሳን አርእስት ይዟል። በዚህ መሠረት ከዚህ ትምህርት በኋላ ሠልጣኞች ሊጨብጡት ይገባል ተብሎ የሚታሰበው ወይም ዋና ዋናዎቹ የክፍል ትምህርቱ ሥልጠና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የነገረ ቅዱሳንን ትርጉም ያስረዳሉ
- የቅዱሳንን ሕይወት መገለጫዎች ይዘረዝራሉ
- የቅዱሳን አሰያየም መንገድን ሁኔታን ያብራራሉ፤
- የቅዱሳንን ማንነት ይገልጻሉ፤
- የቅዱሳንን አስተዋጽኦ ይናገራሉ፤
- ከኢትዮጵያውያን ቅዱሳን የተወሰኑትን ይዘረዝራሉ፤

ከዚህም በተጨማሪ በረከተ ቅዱሳንን ለማግኘት መንገዶችና መነሳሳት እንዲፈጠርና የቅድስና ሕይወት በታሪክነት ብቻ የሚነገር ሳይሆን እያንዳንዳቸውንም በቅድስና ሕይወት እንድንኖር የተጠራንበት ሕይወት መሆኑን በመረዳት ሠልጣኞች ለተቀደሰ ሕይወትና ኑሮ መሠረት /መነሻ/ እና ምሳሌያዊ ወይም አመላካች የክርስትና ሕይወትን ይቀስመበታል ተብሎ ይታመናል። በዚህ መሠረት የእውቀት ፣ የአመለካከትና የክህሎት /የችሎታ የሥራ/ ለውጥ እንዲመጣ /ለማምጣት/ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ አደራ እንላለን።

ነገረ ቅዱሳን

2. 1. ትርጉም

ነገረ ቅዱሳን ከሁለት ቃላት የተገኘ ነው። እነዚህም #ነገር$ እና #ቅዱሳን$ የሚባሉት ቃላት ናቸው። የእያንዳንዳቸውን ትርጉም ለየብቻ እናያለን

<u>ነገር ፦-</u> ማለት በዚህ አገባቡ ትምህርት ማለት ነው፤

<u>ቅዱስ ፦-</u> ለአንድ ወይም ለነጠላ ቁጥር ሆኖ የከበረ ፣ የነጻ ፣ የተባረከ ፣ የተለየ ፣ የተመሰገነ ፣ የተወደደ ማለት ነው።

<u>ቅዱሳን ፦-</u> ለብዙ ቁጥር ሆኖ የከበሩ ፣ የነጹ ፣ የተለዩ ፣ የተባረኩ ፣ የተመሰገኑ ፣ የተወደዱ ማለት ነው። በባሕርዩ ቅዱስ የሆነ እግዚአብሔር በረድኤት ያደረባቸውና በጸጋ የተዋሐዳቸው ሁሉ ቅዱሳን ይባላሉ።

<u>ነገረ ቅዱሳን ወይም ትምህርተ ቅዱሳን፦-</u> ማለት በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ስለ ተከበሩ ፣ ስለ ነጹ ፣ ስለ ተባረኩ ፣ ስለ ተለዩ፣ ስለ ተመሰገኑ ፣ ስለ ተወደዱ ሁሉ የሚሰጥ ትምህርት ወይም ስለ እነሱ ማንነትና ታሪክ የሚናገር ትምህርት ነው። ቅዱሳን የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫዎች እንደመሆናቸው ሁሉ ነገረ ቅዱሳንም ነገረ እግዚአብሔር ነው ማለት ይቻላል።

3. <u>2. የቅዱሳን ሕይወት</u>

የቅዱሳን ሕይወት መገለጫዎች ብዙ ናቸው። እግዚአብሔር በባሕርዩ ቅዱስ ነው። እነሱ ደግሞ በጸጋ ከእግዚአብሔር አግኝተው ቅዱሳን ናቸው። #እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝንና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ$ ዘሌ.19÷2 1÷15-16 በማለት የጠራቸውን አምላክ ድምጽ ሰምተው በዚች ምድር ላይ በኖሩበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘታቸው ሕይወታቸው ያማረና የተወደደ ነው። ሕይወታቸውንና አኗኗራቸውን በጥቂቱ ለመናገር ያህል፦-

ሀ. ከነውር ወይም ከአሳፋሪ ነገሮች ከኃጢአት የራቁ ናቸው። ዕብ.12÷1-5 1ዮሐ.3÷9 ፣ ፊል 2÷14-15

ለ. መላ ዘመናቸውን ከሠይጣንና ከኃጢአት ጋር በመዋጋት በመጋደል የኖሩ ናቸው። ኤፌ.6÷10-19 ፣2 ቆሮ 10÷3-6 ሮሜ 6÷13

ሐ. ስለ ሃይማኖታቸው ብዙ መከራ የተቀበሉ ናቸው። ዕብ.11÷33-38 ፣ 2 ቆሮ.11÷22-29

መ. ክርስቶስ አምላካቸውን የመሰሉት ናቸው። 1 ቆሮ 11÷1 ፣2 ጴጥ 3÷11-12 ይህም በሥልጣን ተካክሉት ማለት አይደለም። እሱ በቃልም በሥራም ያሳያቸውንና ያስተማራቸውን በኑሮአቸው ሁሉ በተግባር አዋሉት ማለት ነው እንጂ። እሱም ሐሳባቸውንና ተጋድሎአቸውን ምክንያት አድርጎ አከበራቸው አጸደቃቸው። ሮሜ.8÷28-31

ሠ. መስቀሉን ተሸክመው የኖሩና በመስቀሉም ኃይል ዓለምን ያሸነፉ ናቸው። በጸና እምነታቸውና በቀና ምግባራቸው ኃጢአትን ድል በማድረግ ከፈጣሪያቸው ክብርን የተቀበሉ ናቸው። 1 ዮሐ 5÷3-6 ፣ ገላ.6÷14

ይህንና ይህን በመሳሰሉ የተጋድሎ ሕይወት የኖሩትን ነው ቅዱሳን የምንላቸው። ከአኗኗራቸውም በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለቅድስናቸው መታወቂያ ብዙ ተነግሮላቸዋል። ጥቂቶችን ብንመለከት ፦-

- #በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ።$ (ማቴ 13÷43 ፣ ዳን.12÷3)
- #እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።$ (ማቴ.5÷14 ፊሊጵ.2÷15-16)
- #እውነት እውነት እላችኋለሁ እናንተስ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአስራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ።$ (ማቴ.19÷28)

እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም በራሱ በእግዚአብሔር ስለ ቅዱሳን የተመሰከረላቸው በአማላጅነታቸው እንድንጠቀም ያስፈልጋል። እንደ እነሱ ያለ የእነሱን የሚመስል ሕይወት መኖር ከቻልን ዛሬም ቅዱስ መሆንና ከቅዱሳን ማኅበር መደመር (መጨመር) ይቻላል።

4. 3. የቅዱሳን አሰያየም

አንድ ሰው ከላይ እንዳየነው ሕይወቱ በንጽሕናና በቅድስና ካማረ በተጋድሎም ከጸና (በጾም በጸሎት ከበረታ) ከቅዱሳን እንደ አንዱ ይሆናል። ቅዱስ የሚለው ስም የሚሰጠው ግን በስብሰባ እንደሚደረገው በእጅ ብልጫ አይደለም። ከላይ እንዳየነው ቅዱሳን የሚያሰኛቸው ሕይወታቸው ነው። በኦሮአቸው ሁሉ ክርስቶስን ከመሰሉ ፣ እንደዘካርያስና ኤልሳቤጥ በእግዚአብሔር ትዕዛዝና ሕግጋት ያለ ነቀፋ ከተጓዙ የቅድስና ባለቤት ይሆናሉ። (ሉቃ.1÷5-6)

የቅዱሳንን ቅድስና መርምራ የምታረጋግጠውና ቅዱስ ብላ የምትሰይመው (ስሙን የምትሰጠው) ቤተክርስቲያን ናት። ቤተክርስቲያን ይህን ሥራ የምትሠራው በቤተክርስቲያኒቱ የበላይ አካል በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት ነው። ሕይወታቸውን መርምራ የምታረጋግጥባቸው ዋና ዋና ነጥቦችም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. #እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን$ (ራእ.2÷10) በተባለው መሠረት በጾም ፣ በጸሎት ፣ በስግደትና በመልካም ሥራ ሁሉ ጸንተው ለሃይማኖታቸው ወደኋላ ሳይሉ የተጋደሉትን ፤

ለ. የቤተክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ጠብቀው የኖሩና ለማስጠበቅ አስፈላጊውን ሁሉ መስዋዕትነት የተቀበሉትን በአገልግሎትም ተግተው የተጋደሉትን፤

ሐ. የእግዚአብሔር ቃል ሳይበረዝ ፣ ሳይፋለስ በማስተማር ያላመነውን ያሳመኑና ፣ ያመነውን ያጸኑትን፤

መ. በሕይወታቸው ነውር (ክፉ ነገር) እና በሃይማኖታቸው ነቀፌታ (ጥርጥር) ያልተገኘባቸውን፤

ሠ. ከዓለም ተለይተው ስለ ክርስቶስ ሲሉ በበረሃ ወድቀው የአጋንንትን ፈተና ፣ የአራዊትን አስፈሪነት የሌሊቱን ጨለማነት ሳይፈሩ በጾም በጸሎትና በስግደት ፈጣሪያቸውን በማገልገል የኖሩትን፤

ረ. በእግዚአብሔር ፈቃድና ረዳትነት እውነተኛ ተአምራት የተደረገላቸውን (ያደረጉትን)፤ ቤተክርስቲያን ከልደታቸው እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው /ሞታቸው/ ያለው ታሪካቸውን ሕይወታቸውን መርምራ ብቁ ሆነው ስታገኛቸው ቅዱሳን ብላ ትጠራቸዋለች።

እነዚህ ሰዎች የቅድስናን ስም (መዐርግ) ካገኙም፡-

- ስማቸው በቅዱሳን መዝገብ ይጻፋል፤
- ሕዝቡ በይፋ እንዲያውቀው ይቀመጣል፤
- ዐጽማቸው ከተገኘ በክብር ይቀመጣል፤
- ገድላቸው (የሕይወት ታሪካቸው) እና የሠሩት ተአምራት ተጽፎ ይቀመጣል ፣ ይነባባል።
- ጽላት (ታቦት) ተቀርጾ ቤተክርስቲያን ይሠራላቸዋል።
- የመታሰቢያ በዓል ቀን ይከበርላቸዋል፤
- ምእመናን በስመ ክርስትና ይጠሩባቸዋል፤

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ቤተክርስቲያን የቅዱሳንን ቅድስና ካረጋገጠችና ቅዱሳን ብላ ከሰየመቻቸው በኋላ ክብራቸውን ለመግለጥ የምታከናውናቸው ዋና ዋና ሥራዎች (ተግባራት) ናቸው።

5. 4. የቅዱሳን ማንነት

በአጠቃላይ ቅድስና በሁለት የሚከፈል ይሆናል።

1. የባሕርይ ቅድስና

ይህ ቅድስና የእግዚአብሔር ብቻ የሆነ ነው። እግዚአብሔር ምን ጊዜም በባሕርዩ ቅዱስ ነው። ይህም ከላይ እንዳየነው ክቡር፣ልዩ፣ቡሩክ፣ምስጉን ነው ማለት ሲሆን ቅድስናው የባሕርዩ ነው ሲባል ማንም ያልሰጠው የራሱ ሀብት ወይም ገንዘብ ነው ማለታችን ነው።(ኢሳ.5÷16፣ ኢሳ.6÷1-3 ፣ ኢሳ.57÷14-15 ፣ ሉቃ.1÷50 ፣ ራእ.4÷8 ፣ ራእ.6÷10).

2. የጸጋ ቅድስና

ጸጋ ማለት ቸርነት ፣ ምሕረት ፣ በጎነት ፣ ያለ ክፍያ "ዋጋ" የሚደረግ ስጦታ ማለት ነው። በዚህ መሠረት ማንኛውም ከእግዚአብሔር የሚገኝ ሀብት ሁሉ ጸጋ ይባላል። እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠው ስጦታ የባሕርይ ገንዘቡ "የራሱ ሀብት" ከሆነው ነው። የባሕርይ ገንዘቡ ከሆኑት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ ቅድስና ነው። እግዚአብሔርም ቅድስናን ተጋድሎአቸውን ምክንያት አድርጎ አንዳንዶችንም ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ በቸርነቱ ለሰዎች ሰጥቷል፤ ይሰጣልም። ለፍጡራን ሁሉ የቅድስናቸው መገኛ "ምንጭ" ራሱ እግዚአብሔር ነው። #እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝ፤$ ብሎ የባሕርይ ቅድስናውን ከነገረን በኋላ #እናንተም ቅዱሳን ሁኑ$። በማለት ሰዎችን ወደ ቅድስና ሕይወት ሲጠራ እናገኘዋለን። ዘሌ.19÷2 #ሁኑ$ በማለቱም ቅድስናን ገንዘብ ለማድረግ የሰዎች ድርሻ ተጋድሎ ወሳኝና አስፈላጊ መሆኑን አመልክቶናል።

3. <u>ቅዱሳን የምንላቸው እነማንን ነው"</u>

በዚህ በነገረ ቅዱሳን ትምህርታችን ከሌሎች ቅድስና በፊት ከእግዚአብሔር ቅድስና በማስከተል የምናየው የእናታችንን የቅድስተ ቅዱሳን ፣ የንጽሕተ ንጹሐን የድንግል ማርያምን ቅድስና ነው። እሷ ከእግዚአብሔር በታች ከፍጥረታት ሁሉ ደግሞ በክብሯ የላቀች "የበለጠች" ናትና።

<u>የእመቤታችን ቅድስናና ክብር በአጭር ሲገለጽ፦</u>

- አምላክን የወለደች ናት፣
- ጸጋ የተመላች ናት፤ሉቃ 1÷28
- እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር ነው፣
- ከሴቶች ሁሉ "መካከል" የተለየች ናት፣
- የብርሃን "የፀሐይ" መውጫ ምሥራቅ ናት፤
- ወደ መንግሥተ ሰማያት መርታ የምታስገባ ናት፤
- ሰውና እግዚአብሔር የታረቁባት ናት፤
- የነቢያት ትንቢታቸው ናት፤
- የሐዋርያት ስብከታቸው ናት
- የሰማዕታት እናታቸው ናት፣
- የጻድቃን እመቤታቸው ናት፣
- በሁለት ወገን "በሐሳብና በሥጋ" ድንግል ናት፣
- ከመጽነሷም በፊት "ከመውለዷም በፊት ከመውለዷም በኋላ" ድንግል ናት፣
- የድኅነታችን የመዳኛችን ምክንያት ናት፣ ዘፍ 28÷10
- ምድርና ሰማይን ያገናኘች መሰላል ናት፤
- ከልጇዋ ከወዳጇዋ ከመድኃኔዓለም ክርስቶስ ጋር መከራን የተቀበለች ነች፣

- ከመስቀሉ ሥር ያልተለየችና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ ሆኖ የሰጠን የአደራ እናታችን ናት። ዮሐ 19÷25

በጥቅሉ ስለ እሷ ተናግሮ መፈጸም የማይቻል ከመሆኑም ሌላ የቅዱሳን ሁሉ መመኪያቸውና የቅድስናቸው ምክንያት እናታችን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። የሁላችንም መመኪያና መማጸኛ የአሥራትና የቃል ኪዳን እናታችን ስለሆነች #ቅድስት ሆይ ለምኝልን$ እያልን በቃል ኪዳኗና በአማላጅነቷ ልንታመንና ወደ እሷ ልንጸልይ ይገባል። ያለ እሷ ድኅነት የለምና።

ሀ. <u>ቅዱሳን መላእክት፦</u> በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ፣ እግዚአብሔርን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የሚያመሰግኑ እና የሚያገለግሉ ለተልእኮ የሚወርዱና የሚወጡ ምስጋናቸው ምግብ ፣ ኃይልና ዕረፍት የሆነላቸው መንፈሳውያን የእግዚአብሔር ሠራዊት ናቸው። (ራእ.5÷6-14)

ለ. <u>ቅዱሳን ሰዎች፦</u> ለአንድ ዓላማ በተለያየ ተግባርና ተልዕኮ እንዲያገለግሉ እግዚአብሔር የፈጠራቸውና ከተጠሩት ውስጥ ፈቃደኝነታቸውን ምክንያት አድርጎ የመረጣቸው ናቸው። (1 ቆሮ 12÷27-31) እነዚህንም በአስር ክፍል ማየት ይቻላል፤

1. <u>ቅዱሳን ነቢያት፦</u> እግዚአብሔር እንደወደደ የገለጠላቸውን ወደፊት የሚሆን ነገር (ክስተት) በእርግጠኝነት የተናገሩና እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም እንደሚወለድ (ሰው እንደሚሆን) የመሰከሩ ናቸው። <u>ለምሳሌ፦</u> ነቢዩ ኤልያስና ነቢዩ ኢሳይያስ.....
2. <u>ቅዱሳን ሐዋርያት፦</u> ክርስቶስ ኑ ተከተሉኝ ብሎ ያስከተላቸውና ከእሱ ተምረው ወንጌልን በመላው ዓለም የሰበኩ የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ናቸው። <u>ለምሳሌ፦</u> ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ
3. <u>ቅዱሳን ጻድቃን፦</u> መላ ዘመናቸውን ስለመንግሥተ ሰማያት (ክርስቶስ) ከዓለም ርቀው በጾም ፣ በጸሎት ፣ በስግደት የኖሩ እውነተኞች ሰዎች ናቸው። ለምሳሌ፦ አቡነ ተክለይማኖት ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ቅድስት ክርስቶስ ሰምራ.....
4. <u>ቅዱሳን ሰማዕታት፦</u> እግዚአብሔርን አንክድም፤ ጣኦት አናመልክም በማለት በከሀድያን ነገሥታት ፊት ቀርበው ሳይፈሩ ስለክርስቶስ የመሰከሩና መከራን ተቀብለው ሕይወታቸውን ስለ ሃይማኖታቸው የሰጡ ናቸው። ለምሳሌ፦ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፣ ቅዱስ መርቆሬዎስ ፣ ቅድስት አርሴማ ....
5. <u>ቅዱሳን አበው (አባቶች)፦</u> የሃይማኖት መጽሐፍ ሳይጻፍላቸውና መምህር ሳይላክላቸው ከቤተሰቦቻቸው በቃል ያገኙትንና በሥነ ፍጥረት መርምረው የተረዱትን መሠረት በማድረግ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ የእግዚአብሔር ወዳጆች ናቸው። ለምሳሌ፦ አባታችን አብርሃምና እናታችን ሣራ፤

6. <u>ቅዱሳን ነገሥታት፦</u> በሥልጣናቸው ፣ በገንዘባቸው ፣ በሠራዊታቸው ሳይመኩ ሃይማኖታቸውን በእግዚአብሔር ላይ አድርገው ድሃ እንዳይበደል ፍርድ ፍትሕ እንደይጓደል ተጠንቅቀው ሕዝቡን በሰላምና በፍቅር የመሩ ያገለገሉ ጉቦ ሳይቀበሉና ሳያዳሉ ያስተዳደሩ ናቸው። ለምሳሌ፦ አፄ ካሌብ ፣ ቅዱስ ላሊበላ፤

7. <u>ቅዱሳን ሊቃውንት፦</u> ምእመናንን በሃይማኖት ያጸኑ ፣ ያላመነውን አስተምረው ያጠመቁ፤ መናፍቃንን ተከራክረው ያሸነፉ ቅዱሳት መጻሕፍትን የጻፉና የተረጎሙ ይህን ሲያደርጉ ብዙ መከራና ስቃይ ስለ ሃይማኖታቸውና ስለ ቤተክርስቲያን አንድነት የተቀበሉ ናቸው። ለምሳሌ፦ ቅዱስ አትናቴዎስ ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ቅዱስ ያሬድ

8. <u>ቅዱሳን ጳጳሳት፦</u> የእግዚአብሔርን ሕዝብና ቤተክርስቲያን በሃይማኖትና በሥርዓት የጠበቁና የመሩ ስለ ክርስቶስ ብዙ መከራ የደረሰባቸውና ወደ ኋላ ሳይሉ የጸኑ ናቸው። ለምሳሌ፦ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፣ አቡነ ጴጥሮስ ኢትዮጵያዊው .....

9. <u>ቅዱሳን መነኮሳት ፦</u> የዓለምን ነገርና ሕገ ጋብቻን ስለ ክርስቶስ ሲሉ ትተው ሥጋዊ /እንስሳዊ/ ጠባይን አሸንፈው በንጽሕና በመኖር እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ ተጋዳዮች ናቸው። ለምሳሌ፦ አባ እንጦንስ ፣ አባ መቃርስና አባ አረጋዊ .....

10. <u>ቅዱሳት አንስት፦</u> ክርስቶስን ለማገልገል ወስነው የተከተሉት በጾም ፣ በጸሎት ፣ በስግደት ጸንተው መከራውን ሳይፈሩ ሕይወታቸውን ሁሉ ስለ ሃይማኖታቸው የሰጡ ሴቶች ናቸው። ለምሳሌ፦ ማርያም መግደላዊት ፣ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ .....

ሐ. <u>ቅዱሳን መካናት</u>

እግዚአብሔር ስሙ እንዲጠራባቸውና እንዲቀደስባቸው የመረጣቸውና በረድኤት ያደረባቸው ቦታዎች ፣ ገዳማትና አድባራት ናቸው። መዝ.64÷5 ፣2 ዜና 7÷12-17 2 ጴጥ.1÷18 <u>ለምሳሌ፦</u> ደብረ ሲና ፣ ደብረ ታቦር ፣ ደብረ ሊባኖስ ወዘተ.....

መ. <u>ቅዱሳት መጻሕፍት</u>

ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈባቸውና ቤተክርስቲያን ቆጥራ የተቀበለቻቸው ናቸው። <u>ለምሳሌ፦</u> የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስ 2 ጴ.1÷20-21

ሠ. <u>ቅዱሳት ሥዕላት</u>

ሥጋዊውን ዓለም ከሚያንጸባርቁ ዓለማውያን ሥዕላት ፈጽመው የተለዩ የእግዚአብሔር ፣ የእመቤታችን ፣ የነቢያት ፣ የሐዋርያት ፣ የጻድቃን ፣ የሰማዕታት ፣ የመላእክት ፣ የቅዱሳን ሁሉ ውክልና ያላቸው ሆነው ቤተክርስቲያን

የምትቀበለውን የአሣሣል መንገድ ተከትለው የተሣሉ ሥዕሎች ናቸው። ለምሳሌ ፦ የሥላሴ ሥዕል ፣ የእመቤታችን ሥዕል ፣ .....

ረ. ቅዱሳት ዕለታት

እግዚአብሔር ራሱን የገለጠባቸውና ድንቅ ሥራ የሠራባቸው ዕለታት የተቀደሱ ናቸው። ቅዱስ ዳዊት #ለጌትነቱ ለተአምራቱ መታሰቢያን አደረገ$ እንዳለ (መዝ.110÷4) ይህም ሥራ የሠራባቸው ዕለታት እንድናከብራቸው ያሳስበናል። በኦሪት ዘፍጥረትም እግዚአብሔር ሰባተኛዋን ቀን ባረከት ፣ ቀደሳትም ሊፈጥረው ከጀመረው ሥራ ሁሉ በእርስዋ ዐርፎአልና። የሚል ስለ ቀዳሚት ሰንበት ቅስድና የተጻፈ መረጃ እናገኛለን። (ዘፍ.2÷3) ስለ እሑድ (ሰንበተ ክርስቲያን) ደግሞ #በእሑድ (በጌታ ቀን) ቀን መንፈስ ቅዱስ ወደ እኔ መጣ$ በማለት ክርስቶስ ከሙታን በተነሣባት በዚች የተቀደሰች ዕለት የተገለጠበትን ምሥጢር መጻፍ ይጀምራል። (ራእ.1÷10) እነዚህና ሌሎችም እግዚአብሔር ራሱና በእናቱና በወዳጆቹ አድሮ ሥራ የሠራባቸው ዕለታት ሁሉ ቅዱሳት ናቸው።

ሰ. ቅዱሳት ንዋያት /ንዋየ ቅድሳት/

በቤተክርስቲያን ውስጥ ለአገልግሎት የሚውሉ ንዋያት (ዕቃዎች) ሁሉ የተቀደሱ ናቸው። ወደ ቤተክርስቲያን ገብተው አገልግሎት ሳይጀመርባቸው በፊት በጳጳሳት ወይም በካህኑ ተገቢው ጸሎት ተደርጎ ይባረካሉ። በቅብዐ ሜሮን ይከብራሉ (ይቀደሳሉ)። ከዚህ በኋላ ለተቀደሰው አገልግሎት ይውላሉ።(ዘፍ.40÷1-12)

በጥቅሉ እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ የእርሱና ለእርሱ የሆነ ሁሉ በእርሱ ቸርነት የተቀደሰ ነው። ይህን የፍጡራን ቅድስና የምታረጋግጠውና የምታውጀው ቤተክርስቲያን መሆኗን ማወቅና ራሷም ከሌሎች በፊት ቅድስት መሆኗን መዘንጋት አይገባም። (ኤፌ.5÷26-28)

6. 5. የቅዱሳን አስተዋጽኦ

የቅዱሳን አስተዋጽኦ ከምንም በላይ የሚታወቀውና ጎልቶም የሚነገረው መንፈሳዊውና ሰማያዊው ነው። ለምሳሌ ያህል፦

- በአማላጅነታቸው ነፍሳት ከሲኦል መዳናቸውና
- በቃል ኪዳናቸው ምእመናን ከስቃይ መትረፋቸውን መጥቀስ ይቻላል።

በሥጋዊው ዓለምም ተነገሮ የማያልቅ ጥቅም (አስተዋጽኦ) አላቸው። በዚህ ዓለም ቅዱሳን ከሌሉ የእግዚአብሔርን ጸጋና በረከት ከማጣታችንም በላይ የምንኖርባት ምድር ለጥፋት የቀረበችና የተዘጋጀት ትሆናለች ወይም ትጠፋለች። በሎጥ ዘመን የነበሩት ሰዶምና ገሞራ የሚባሉ ከተሞች 10 ቅዱሳን እንኳን ስላልነበረባቸው እግዚአብሔር አንዱን

ቅዱስ ሎጥንና ቤተሰቡን አድኖ ከተማዎችን እንዳጠፋቸው ተምረናል። ዘፍ.18÷16 ፍጻሜ ፣ ዘፍ.19÷1 ፍጻሜ የቅዱሳንን አስተዋጽኦ አጠር አድርገን በየፈርጁ እንመለከታን።

ሀ. ለሀገር

- ከላይ እንዳየነው ሀገር እንዳትጠፋ ይጠብቃሉ።
  - በጸሎታቸው
  - በምልጃቸው
  - በቃል ኪዳናቸው
- በልማት እንድታድግ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርግዋል፤ ያደርጋሉ።
  - በደን ልማትና በዱር አራዊት ጥበቃ
  - በአዝርዕ ልማት ራስን በመቻል
  - በእንስሳትና ንብ ርባታ
- በቱሪዝም የሀገር ገቢ እንዲዳብር አድርገዋል፤ እያደረጉም ነው።
  - በቅርስ ጥበቃ
  - በታሪክ ገጽታ ግንባታ
  - በአከባቢ ጥበቃ
- ለሰላምና ለአንድነት ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል
  - ሀገር እንዳትወረር
  - ስትወረርም በመከላከል
  - ሕዝቡን በመምራትና ምሳሌ በመሆን

  ለምሳሌ፦ ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ ኢትዮጵያዊው
- ሁለንተናዊ ሕይወቱ የተስተካከለ እና በሥነ ምግባር የታነፀ ዜጋ እንዲኖራት በማድረግ፤
- ከወንጀል የራቀና ሰላማዊ የሆነ
- ውድመትንና ጥፋትን የማይሻ ዜጋን በማፍራት
- ተቻችሎ የሚኖር .....ወዘተ

ለ. ለሕዝብ

- በጾም ፣ በጸሎታቸውና በቃል ኪዳናቸው በመጠበቅ
- የበረከት ምንጭ በመሆን
- ሰላማዊ ሕይወት እንዲኖር በማድረግ

- በሥነ ምግባር እንዲታነጹ በማስማርና ሞዴል በመሆን
- በጸበላቸው ፣ በመካነ መቃብራቸው ፣ በገድላቸው
  - ሕሙማንን በመፈወስ
  - ልጅ ላጡ ልጅ በመስጠት
  - ሥራ ላጡ ሥራ በመስጠት
- በኪነ ጥበብ መምህር ምሳሌ በመሆን
  - በሥነ ጽሑፍ
  - በሥነ ሕንፃ
  - በሥነ ሥዕል
- ሥራ ወዳድና ፈጣሪ እንዲሆኑ በማስተማርና በማሳየት
- እርስ በእርስ እንዲዋደዱ አስተምሮና ኖሮ በማሳየት
- መረዳዳትንና መተዛዘንን ሠርቶ በማሳየ በማስተማር

ይህንና ይህን በመሳሰሉ በርካታ ተግባራት በቃልና በሕይወት በኑሮ በማስተማር ሕዝቦች በዚህ ዓለም በሰላም ፣ በፍቅር ፣ በበረከት ፣ በጤንነትና በአንድነት እንዲኖሩና ሰማያዊቷን ርስት መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርሱ በማስቻል ረገድ ቅዱሳንና ቅዱሳት በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፤ ወደፊትም ያበረክታሉ። የቅዱሳን ወይም የቅዱሳት አስተዋጽኦ ጥቅም ስንል ከላይ የዘረዘርናቸውን ሥራዎቻቸውንና የተቀሩትም አስተዋጽኦዎቻቸውን ሁሉንም የሚመለከት እንጂ ቅዱሳን ሰዎችን ብቻ ማለታችን አይደለም።

7. 6. ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን /ቅዱሳት/

ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ሀገረ እንደመሆኗ መጠን የቅዱሳንም ሀገር ነች። በሀገራችን በኢትዮጵያ ቁጥራቸው ከመብዛቱ የተነሣ ብዛታቸው የማይታወቅ እጅግ በጣም ብዙ ቅዱሳንና ቅዱሳት አሉ። በጣም ጥቂቶቹን ብቻ ለማሳያ እንዲሆነን እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

ሀ. **ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፦** በ34 ዓመተ ምሕረት ክርስትናን በፈቃደ እግዚአብሔር ከቅዱስ ፊሊጶስ ተምሮ ወደ ኢትዮጵያ ያመጣልን የመጀመሪያው ሐዋርያችን "መምህራችን" ነው። "ሐዋ.8÷26-40" ስሙ አቤላክ ባኪ ሲሆን ከሀገራችን ከኢትዮጵያ ጀምሮ በየመን ፣ በፐርሽያ ፣ በሕንድ እና በአከባቢያቸው እያስተማረ እስከ ቻይና አቅራቢያ ሐዋርያዊ ጉዞ ያደረገና በሰማዕትነት ያረፈ ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ ያመጣ አባታችን ነው።

ለ. **አብርሃና አጽብሐ ፦** በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአንድነት ነግሠው ኢትዮጵያን በሰላምና በፍቅር ያስተዳደሩ ወንድማማች ነገሥታት ናቸው። ከሕዝብ አስተዳደሩ ጎን ለጎን በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን ያሠሩ ሕዝቡን የክርስትና ሃይማኖት ያስተማሩ በዘመናቸው ሁሉ ሰውን ሳይበድሉና እግዚአብሔርን ሳያሳዝኑ የኖሩ ናቸው።

ሐ. <u>ቅዱስ ያሬድ፡-</u> በ 6 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እግዚአብሔር ያስነሣው ፣ የመላእክት ዝማሬ የገለጸለት ታላቅ አባት ነው። የቤተክርስቲያናችን የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድ ከእግዚአብሔር አግኝቶ ባቆየልን ዜማ (ዝማሬ) ቤተክርስቲያን አሁንም ለዘለዓለሙ ትገለገልበታለች። ከሱ የዜማ ስልት የወጣ (የተለየ) ሁሉ የቤተክርስቲያናችን የዝማሬ መገልገያ መሆን አይችልም።

መ. <u>አቡነ አረጋዊ፡-</u> ከሮም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢትዮጵያን ሀገራቸው አድርገው በቅድስና ሕይወት የኖሩ ከተለያዩ ሀገሮች እንደሳቸው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ 8 ቱ ቅዱሳን ጋር በርካታ መንፈሳዊ ሥራ የሠሩ ታላቅ አባት ናቸው። ሁሉም (ዘጠኙም)

- ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ያጸኑ፤
- መጻሕፍትን የተረጎሙ ፣
- ስብከተ ወንጌልን ያስፋፉ፣
- ገዳማትን የመሠረቱ፣
- የምንኩስናን ሥርዓት ያሳዩና ያስተማሩ ናቸው፤

አቡነ አረጋዊ በትግራይ ክልል ደብረ ዳሞ ከሚባል ተራራ ዘንዶ ተሸክሞ ያወጣቸውና ገዳም መስርተው የተጋደሉ በቅድስናም ኖረው የተሰወሩ አባት ናቸው።

መ. <u>ቅዱስ ላሊበላ፡-</u> የተመሰገነ ክርስቲያናዊ ሕይወት የነበረው በኢትዮጵያ ንጉሥ ሆኖ ከመንገሡ በፊትም ሆነ ከነገሠ በኋላ እግዚአብሔርን በመፍራት የኖረ ከባለቤቱ (ከሚስቱ) ከቅድስት መስቀል ክብራ ጋር በተቀደሰ አኗኗር እግዚአብሔርን እያገለገለ የኖረ ነው። ድሀ እንዳይበደል ፍርድም እንደይጓደል እየተጠነቀቀ ሕዝቡን በሰላም ከመምራቱም በላይ በመንፈሳዊው ሕይወት ረገድ በጾም ፣ በጸሎት ፣ በስግደት ጸንቶ የኖረ 11 ፍልፍል (ከድንጋይ የተፈለፈለ) አብያተ ክርስቲያናትንና ሌሎችንም በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን የሠራ ያሠራ ጻድቅ ንጉሥ ነው። በመላው ዓለም የታወቁትና በብዙ ሺኽ የዓለም ሕዝቦች ዛሬም እየተጎበኙ ያሉት የሥራ ውጤቶች ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት በላሊበላ ከተማ ይገኛሉ።

ረ. <u>አቡነ ተክለሃይማኖት፡-</u> ከ 12 ኛው - 13 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት ጻድቁ አባታችን የኢትዮጵያ ሐዋርያ ፣ የኢትዮጵያ ፀሐይ ፣ አዲስ ሐዋርያ በመባል ይታወቃሉ። በጾም ፣ በጸሎት ፣ በስግደት ፣በስብከተ ወንጌልና በቅድስና ሥራዎች ሁሉ ፍጹም ይተጉ የነበሩት አባታችን ከኢትዮጵያ ጣኦት አምልኮን ለማጥፋት የታገሉና የተሳካላቸው ቅዱስ ነበሩ። መላ ኢትዮጵያን በተለይም ወላይታንና አካባቢውን ሁሉ እንዲሁም የሸዋን ምድር በሞላ ዞረው ያስተማሩ የሁላችንም አባት ናቸው። ዞሮ ማስተማር ሲያቅታቸው ከዋሻ ገብተው 8 ጦሮችን በዙራያቸው ስለቱን ወደራሳቸው አድርገው በአራት አቅጣጫ ሁለት ሁለቱን

ተክለው በሁለት እግራቸው ሳያርፉ ከ 15 ዓመት በላይ ቆመው የጸለዩ ፣ አንድ እግራቸው ሲቆረጥ በአንድ እግራቸው 7 ዓመት ቆመው ሳያርፉ በመጸለይ የተጋደሉ ፣ እግዚአብሔር የጸጋ ክንፍ የሰጣቸው አባት ናቸው። ዛሬ አጽማቸው ለአዲስ አበባ ቅርብ ከሆነ ቦታ ደብረ ሊባኖስ በሚባል ገዳማቸው በክብር ዐርፎ ይገኛል።

ሰ. <u>ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ፡-</u> በተቀደሰ ጋብቻ በትዳር ትኖር የነበረች እናት ነች። በትዳሯ እግዚአብሔርን ደስ ታሰኝ የነበረች 12 ልጆች የወለደች ስትሆን በኋላ ግን ቤቷንና ልጆቿን ትዳሯን ፣ ቤተሰቧን ትታ የመነነች ወደ በረሃ፣ ገዳም የገባች ቅድስት እናታችን ነች። እንደ አቡነ ተክለሃይማኖት እሷም ጉድጓድ አስቆፍራ 12 ጦሮች ተክላ 12 ዓመት የኖረች ናት። አስቀድማም በባሕር ውስጥ ገብታ ወዲያ ወዲህ ሳትል ስለክርስቶስ 12 ዓመት ኖራለች። የተወለደችው አቡነ ተክለሃይማኖት በተወለዱበት ሀገር በሸዋ ቡልጋ ውስጥ ሲሆን ዕረፍቷ ጎጃም ከጣና ደሴቶች አካባቢ ጓንጉት ከመትባል ቦታ ነው።

ሸ. <u>አቡነ ተጠምቀ መድኅን ፡-</u> በ 17 ኛው መቶ ክፈለ ዘመን የነበሩ እኝህ ታላቅ አባት በልጅነታቸው በእረኝነት ከብት ሲጠብቁ የሚሰጣቸውን ምግብ ለመንገደኞችና ለድሆች በመስጠት በጾምና በጸሎት መኖርን የጀመሩ ከብቶቻቸውን በዱር ትተው በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ገዳም በመሄድ ይማሩ የነበሩ ናቸው። ከብቶቻቸው ከአራዊት ጋር እየቦረቁ ውለው በነብርና በተኩላ እየተነዱ ወደ ቤታቸው የሚገቡላቸው ቅድስናን ገንዘብ ያደረጉ አባት ናቸው። በቻግኒና አካባቢው በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን የመሠረቱና ሕዝቡን በማስተማር በክርስትና ሃይማኖት ያጠመቁ አባት ናቸው። የጋዝጌን ሕዝብ እና በምዕራብ ኢትዮጵያ ጠረፋማ አካባቢ እስከ ሱዳን ድንበር ድረስ ተዘዋውረው የክርስቶስን ወንጌል የሰበኩ ታላቅና ቅዱስ አባታችን ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ ከቅዱሳት አንስታት ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ፣ ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ ፣ ቅድስት አመተ ክርስቶስንና የመሳሰሉትን ጨምሮ በርካታ ኢትዮጵያውን ቅዱሳንና ቅዱሳት በቤተክርስቲያናችን የክብር መዝገብ ተመዝግበው ይከበራሉ።

8. ማጠቃለያ

ስለ ቅዱሳን /ቅዱሳት ይህን ያህል በጣም በአጭር ለማየትና ለመማር ከቻልን ቀሪውን ወደፊት ተጨማሪ መጻሕፍትን በማንበብ የበለጠ ለማወቅና ለመጠቀም መታገል መጣር ይጠበቅብናል።

እግዚአብሔር ጸጋውንና ዕድሜውን ከሰጠን ስለቅዱሳን መማርና ማወቅ ብቻ ሳይሆን በቅዱሳን አማላጅነትና ቃል ኪዳን ተጠቃሚዎች ለመሆን አቅም የፈቀደውን ሁሉ ማድረግ አለብን።

- በስማቸው ቤተክርስቲያን በመሥራት፣ኢሳ.56÷4-8
- ለጸጋ ቅድስናቸው የጸጋ ስግደት በመስገድና የሚገባቸውን ክብር በመስጠት፤
- መታሰቢያቸውን በማድረግና በስማቸው ምጽዋት በመስጠት፤
- በስማቸው በፈለቁ ጸበሎች በመጸበል በመጠመቅ፤
- ስማቸውን ጠርቶ አምላክ ቅዱሳን እግዚአብሔርን በመማጸን፣
- የቅድስና ሕይወታቸውን ምሳሌ በማድረግ ሃይማኖትን መጠበቅና ማጽናት እንዲሁም የመሳሰሉት መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥቅሞች መካፈል ያስፈልጋል።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን

9. ዋቢ ማጣቀሻ መጻሕፍት

1. ነገረ ቅዱሳን ቁጥር 1 ለግቢ ጉባኤያት የተዘጋጀ ፤ ማኅበረ ቅዱሳን 2001 ዓ.ም
2. ነገረ ቅዱሳን ቁጥር 2 ለግቢ ጉባኤያት የተዘጋጀ፤ ማኅበረ ቅዱሳን 1998 ዓ.ም
3. ክብረ ቅዱሳን ፣ አባ ገብርኤል፤ 1990 ዓ.ም፤አዲስ አበባ
4. ክብረ ቅዱሳን ፤ ቀሲስ ከፍያለው መራሒ፤ 1999 ዓ.ም፤አዲስ አበባ
5. ፍኖተ ቅዱሳን ፤ ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ፤1995 ዓ.ም፤ አዲስ አበባ
6. ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ ፤ መ/ር ገ/ማርያም እሸቴ፤ 1992 ዓ.ም፤አዲስ አበባ
7. ቅዱሳት ሥዕላት ፤ ሚሊዮን በለጠ ፤ 1994 ዓ.ም፤ አዲስ አበባ
8. መፍሐፍ ቅዱስ ፤ የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን፤2000 ዓ.ም፤አዲስ አበባ